# መልካም አስተዳደር የእድገታችን መሰረት ነው!

አዲስዓለም ታዬ

ትግራይ ኦንላይን April 22, 2014

ጠንካራ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርዓት ለመፍጠር ከሚያድፈልጉት ቁልፍ ጉዳዮች መካከል ቀዳሚ ሊባል የሚችልው መልካም አስተዳደር እንደሆነ የማህበረሰብ ሳይንስ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ በእነዚህ ምሁራን ምልከታ መሰረት በመንግስትና ህዝብ መካከል በመተማመንና በመተጋገዝ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ሊፈጠር የሚችለው የመንግስት ስርዓቱ አስተማማኝ የመልካም አስተዳደር ሁኔታን መገንባት ሲችል ብቻ ነው፡፡ መልካም አስተዳደር የሚገለፅባቸው ሁኔታዎች በርካታ ናቸው፡፡

የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የህግ የበላይነት፣ ተጠያቂነት፣ ፍትሃዊነት፣ አሳታፊነትነና ግልጽነት ዋነኛዎቹ የመልካም አስተዳደር መገለጫዎች መሆናቸውን ያትታል፡፡ ኮሚሽኑ በማያያዝም ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች የሚገለፁበት መልካም አስተዳደር በማንኛውም አገር ውስጥ ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትንና አገራዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚያስችል መሳሪያ መሆኑንም ይጠቁማል፡፡

መልካም አስተዳደር በሰፈነበት አገር ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የተረጋገጠ በመሆኑ የዜጎች ቅሬታ በእጅጉ ይቀንሳል፤ የዚህ ዓይነቱ አስተዳደር የዜጎችን ሁለንተናዊ አገራዊ ተሳታፊነትና ባለቤትነት የሚያረጋግጥ በመሆኑ የሚወጡኑ የመንግስት የልማትም ሆነ ሌሎች አገራዊ ፋይዳ ያላቸው ፖሊሲዎች ህዝባዊ መሰረትን ይጎናፀፋሉ፤ ይህም ዜጎች ለአገር የሚጠቅም እስከሆነ ድረስ በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ጉዳት የሚያስከትልባቸው ቢሆንም እንኳ የመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሳኩ የሚጠበቅባቸውን ድጋፍ ሁሉ ከማድረግ ወደኋላ የማይሉበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ዜጎች ከመንግስት የሚጠብቋቸው የተለያዩ አገልግሎቶችን በሚፈልጉት ጥራት፣ ፍጥነትና ብቃት ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ የሚፈጠረው ጠንካራ መልካም አስተዳደር በሰፈነበት ስርዓት ውስጥ ነው፤ የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ደግሞ በህዝብና በመንግስት መካከል ጠንካራ መተማመንን እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ ሰላምና መረጋጋት እንዲጠናከር፣ እድገትና ብልጽግና እውን እንዲሆን፣ በተጋገዝና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ አገራዊ አንድነትን ለማምጣት መልካም አስተዳደር ሁነኛው መንገድ ነው፡፡

መልካም አስተዳደርን ሙሉ በሙሉ እውን ከማድረግ አኳያ ከላይ የተጠቀሱት የመልካም አስተዳደር መገለጫዎችን በተናጠል ማየት ያዳግታል፡፡ እያንዳንዱ የመልካም አስተዳደር መገለጫ በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ እርስ በእርሱ የተቆራኘ በመሆኑ አንዱን ከሌላው ነጥሎ ማየት አግባብ አይሆንም፡፡ ያም ሆኖ ግን የዚህ አጭር አስተያየት ዓላማ የህዝብ አገልግሎትን በፍጥነት፣ በጥራትና ፍትሃቀዊ በሆነ መንገድ ለዜጎች ማቅረብ አለመቻል መልካም አስተዳደርን ለማጠናከር በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሚፈጥረውን እንቅፋት በተመለከተ ያለኝን ምልከታ ማካፈል ይሆናል፡፡

እላይ በጥቂቱ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ዜጎች ከመንግስታቸው የሚጠብቁትን መሰረታዊ አገልግሎት በአግባቡ ማግኘት ካልቻሉ በመንገስታቸው ላይ ያላቸው እምነት ይሸረሸራል፣ መነገስታቸው የሚወጥናቸውን የልማትም ይሁን ሌሎች ፖሊሲዎች ለማስፈጸም የሚኖራቸው ተነሳሽነት በእጅጉ

ይቀንሳል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ከመሻሻል ይልቅ እየተባባሰ የሚሄድ ከሆነም አገርን ሰላምና መረጋጋት በማሳጣት ቀውስ ውስጥ ሊከት እንደሚችል በተለያዩ ምሁራን የቀረቡ ጥናቶች በተጨባጭ አረጋግጠዋል፡፡

በኢትዮጵያ የዚህ ዓይነቱ ችግር እንዳይፈጠር የሚያስችሉ የተለያዩ እርምጃዎች ተወስደዋል፤ በመወሰድም ላይ ናቸው፡፡ በአገራችን በተለይ አዲስ ዓይነት የፖለቲካ ስርዓት ከተመሰረተበት ካለፉት 20 ዓመታት ወዲህ በርካታ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዎ ለውጦች በስፋት እየታዩ ስለመሆናቸው የብዙዎቻችን ትዝብት ነው፡፡

ለዚህ ለውጥ እውን መሆን መሰረታዊውን ሚና እየተጫወተ ያለው ደግሞ ፌዴራላዊው የአገሪቱ ህገ መንግስት መሆኑን በአገሪቱ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ያካሄዱ የተለያዩ አካላት የሚገልፁት እውነት ነው፡፡ ይህ ህገ መንግስት ትልቅ ትኩረት ከሰጣጠው ጉዳዮች መካከል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የመልካም አስተዳደር ሁኔታን የተመለከቱ ናቸው፡፡ የአገሪቱ የተለያዩ ፖሊሲዎችም በአገሪቱ የፖለቲካ መረጋጋትም ይሁን የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ማረጋገጥ የሚቻለው ጠንካራ የመልካም አስተዳደር ሁኔታ ሲፈጠር መሆኑን አፅንኦት ይሰጣሉ፡፡

ከዚህ አንጻር ይመስላል መንግስት መልካም አስተዳደር ይጠናከር ዘንድ የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ መሆኑን ይገልፃል፡፡ እኔ እንደታዘብኩት ከሆነ መንግስት ይህንን እርምጃ የሚወስደው የተለያዩ ተቋማዊ ስርዓቶችን በመፍጠር ጭምር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሊነሱ የሚችሉት ትላልቅ ተቋማት የሰብአዊ መበት ኮሚሽንና የእንባ ጠባቂ ተቋም ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ በአገሪቱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አማካኝነት በተለያዩ የአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ላይ በሚካሄድ የክትትል ተግባርም የመልካም አስተዳደር ጉዳይ ቁጥጥርና ክትትል ሲደረግለትም ይታያል፡፡ በዚህም የተነሳ በእኔ እምነት የመልካም አስተዳደር ጉዳይ የመንግስት አንኳር የትኩረት አቅጣጫ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንን ተከትሎም በአገሪቱ በተለያዩ መልኩ የመልካም አስተዳደር ሁኔታ መሻሻል ይታያል፡፡

እንዲያም ሆኖ ግን በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የመልካም አስተዳደር እጦት እየታየ መሆኑን ዜጎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲገልፁ ይደመጣል፡፡ ይህንን የዜጎች ብሶት የአገሪቱ መንግስት ባለስልጣናትም አምነው የተቀበሉበት ሁኔታ መኖሩንም ታዝቤያለው፡፡ ይህ የመልካም አስተዳደር ችግር የሚታየው ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ በተለይም በከተሞች አካባቢ መንግስት ከሚያቀርባቸው የኤሌክትሪክ፣ የውሃ፣ የስልክና መሰል መሰረታዊ አገልግሎቶች ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ በተለይ በአዲስ አበባ ከመገናኛ ብዙሃን በየቀኑ የሚሰማው ሮሮ ነዋሪው ህዝብ የውሃ፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና የተንቀሳቃሽ ስልክ አገልግሎቶችን በአግባቡ ማግኘት አለመቻሉን የሚገልፁ ናቸው፡፡

ለዚህ ዓይነቱ የህዝብ አገልግሎት እጥረት ምንጭ የተለያዩ ምክንያቶች ድምር ይሆናል የሚል የግል ትንታኔ አለኝ፡፡ ለዚህ አስተያየቴ ያግዘኝ ዘንድ ግን ሁለት መሰረታዊ የሚባሉ ምክንያቶችን ላቅርብ፡፡

በእኔ እምነት አንዱ ምክንያት የሚከተለው ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ችግር በየዘርፉ ከተሰማሩት ባለሙያዎች ወይም የስራ ኃላፊዎች መካከል በሙያ ብቃት ማነስ ወይም የህዝብ አገልጋይነት ስሜት እጦት ወይም ከህዝብ ጥቅም የግል ጥቅምን ማስቀደም ከሚመርጡ ጥቂቶች ጋር ተያይዞ ሊመጣ የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ችግር ደግሞ ጠንካራ የቅርብ ክትትል፣ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን መሰረት ያደረገ የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት ሊከላከሉት የሚችል ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ረገድ ድክመት ስለመኖሩ ለመረዳት በአገልግሎቱ ረገድ አመርቂ መሻሻል አለመታየቱንና በየእለቱ እየጨመረ የመጣውን የነዋሪዎን የእለት ተእለት ብሶት ማጤን ብቻ ይበቃል፡፡

ሌላውና ምናልባትም ዋነኛ የሚባለው ግን በተለይ አዲስ አበባ በህዝብ ብዛት፣ በኢኮኖሚና ሌሎች ረገዶች እያደገችበት ያለችበት ፍጥነትና ከተማዋ መስጠት የምትችለው ማህበራዊ አገልግሎቶች መጠን አለመጣጣሙ ነው፡፡ ይህ በተለያዩ የመንግስት አካላትና የምጣኔ ኃብት ምሁራን ጭምር ተቀባይነት ያለው ምክንያት መሆኑም ይነገራል፡፡

በሁለቱም ምክንያቶች ሳቢያ በመልካም አስተዳደር ዙሪያ የሚታየውን ችግር ለመቅረፍ የተለያዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆናቸውንም ታዝቤያሁ፡፡ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ የተጀመረው እንቅስቃሴ ሰፊና ግቡም ስር ነቀል ለውጥ ማምጣት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ከወራት በፊት ይፋ በሆነ አንድ የከተማው አስተዳደር ሰነድ ላይ እንደተመለከተው የከተማው ባለስልጣናት መልካም አስተዳደርንና የአገልግሎት አሰጣጥን በከፍተኛ ደረጃ ለማጠናከር ሰፊ እንቅስቃሴ መጀመራቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

ይህ እንቅስቃሴ ከቀበሌ ጀምሮ በሁሉም የከተማው አገልግሎት መስጫዎች ላይ የሚያነጣጥር ከመሆኑም በላይ ለመልካም አስተዳደር መጎልበት እንቅፋት የሆኑትን ሙስናን ጨምሮ መሰል ተግባራትን መዋጋት ያካተተ መሆኑን ሰነዱ ያብራራል፡፡ ከግለሰቦችና ከአሰራር ስርዓት ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር በማስወገድ ላይ የሚያተኩረት የከተማው የመልካም አስተዳደር ስትራቴጂ ሰነድ በየተቋሙ የተመደበውን የመንገስት ሰራተኛ አስተሳሰብ በማረቅና ግልጽ፣ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች የማይመች የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት ረገድ ትልቅ ሚና ሊጫወት ይችላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ከዚህ ጎን ለጎንም የከተማው አስተዳደር በአሁኑ ወቅት የህዝብ ሮሮ በመሆን እየተደመጡ ያሉትን የውሃን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶችን ከከተማውና ከህዝቡ የፍላጎት እድገት ጋር የተጣጣመ ለማድረግ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች በስፋት በማከናወን ላይ መሆኑን እየሰማን ነው፡፡ ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል ከእለት ወደእለት እየሰፋ የመጣውን የመጠጥ ውሃ ችግር ለመቀነስ የከተማው አስተዳደር የጀመረውና በመጪው ዓመት መገባደጃ ላይ ይጠናቀቃል ተብሎ የሚጠበቀው ይጠቀሳል፡፡ በቻይና ኩባንያ አማካኝነት በአቃቂ አካባቢ ከአንድ ቢሊዮን በላይ በሆነ ወጪ የሚገነባው የከርሰ ምድር ውሃ ፕሮጀክት በተጠቀሰው ጊዜ ሲጠናቀቅ ከሰባት መቶ ሀምሳ ሺህ በላይ አዲስ የውሃ ጠተቃሚዎችን ማስተናገድ ይችላል፡፡

ከዚህም በላይ የከተማው አስተዳደር አሁን ባሉት የመጠጥ ውሃ አገልግሎት መስጪያዎች ተጨማሪ የመጠጥ ውሃ ማቅረብ ይችሉ ዘንድ የማስፋፋትና የማጠናከሪያ ግንባታ እየተካሄደባቸው መሆኑንም የከተማው ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት መስጫ ተቋም አስታውቋል፡፡ ይህ የማስፋፊያ ፕሮጀክት በራሱ ከ200 ሺህ የሚልቁ ተጨማሪ የመጠጥ ውሃ ደንበኞችን ማስተናገድ የሚችል መሆኑም ተመልክቷል፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብን ተጠቃሚ በማድረግ በከተማው ውስጥ የሚታየውን የመጠጥ ውሃ ችፍግር ሙሉ በሙሉ ያስወግዳሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የስልክና ተያያዥ መሰረተ ልማቶችን ለማጠናከርም ከፍተኛ የሆነ የልማት ስራ በመከናወን ላይ መሆኑን ሰሞኑን አድምጠናል፡፡ ከዚህ የልማት ስራ መካከል የስልክ ኔት ወርክ አቅም ግንባታ ይጠቀሳል፡፡ በአዲስ አበባ ላለፉት ዓመታት ከፍተኛ የስልክ ግንኙነት ጥራት ችግር ይታይባቸው የነበሩት አካባቢዎች ካለፈው ወር ጀምሮ የነበረባቸው ችግር በአንዳንዶቹ ሙሉ በሙሉ በተወሰኑት ዘንድ ደግሞ በከፊል የተቀረፈ መሆኑን ራሳቸው ተጠቃሚዎቹ በመግለጽ ላይ ናቸው፡፡

ይህ የሰሞኑን እርምጃ በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት አውታር ለማጠናከር፣ ለማስፋፋትና ከዓመት ዓመት እያደገ የመጣውን አገራዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት መሰረት ያደረገ እንዲሆን ታስቦ በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ ያለው የቢሊዮኖች ዶላር ፕሮጀክት አካል መሆኑንም መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህ እጅግ ግዙፍ የሆነው የቴሌኮም ፕሮጀክት በአሁኑ ወቅት ያለውን የሽፋንና የጥራት

ችግር ከማስወገድ ባለፈ አገሪቱ የጀመረችውን የኢኮኖሚ እድገት የበለጠ ለማፋጠን የሚያግዝ መሆኑም የታመነበት ነው፡፡

የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎትን በተመለከተም ተመሳሳይ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ አገሪቱ ከጀመረችው ሰፊ የልማት እንቅስቃሴ አንጻር በቂና ዘላቂ የሆነ የኃይል አቅርቦት ለመፍጠር በአባይ ወንዝ ላይ የሚገነባውን የህዳሴውን ጨምሮ ሌሎች የኃይል ማመንጫ ግድቦች በመገንባት ላይ መሆናቸው ከዚህ አኳያ ሊታይ የሚገባው ተስፋ ሰጪ እርምጃ ነው የሚል እምነት አለ፡፡

በከዚህ ባሻገር በአዲስ አበባና በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች የሚታየውን የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ችግር ለማስወገድ ይቻል ዘንድ በአሁኑ ወቅት ያለውን የቴክኒክ ችግሮች ለማስወገድና አገልግሎቱንም በሚፈለገው መጠን፣ ጥራትና የደንበኞችን ፍላጎት ሊያሟላ በሚችል መልኩ ለማቅረብ የሚያስችሉ አፋጣኝ እርምጃዎች በመወሰድ ላይ መሆናቸውንም ከሚመለከታቸው የመንገስት አካላት በመስማት ላይ ነን፡፡

በእኔ እምነት በአሁኑ ወቅት እላይ ከተጠቀሱት አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚታየው ችግር መሰረታዊ ምንጭ አገልግሎቶቹ ከከተማው ህዝብ ቁጥር እድገትና በመዲናዋ ከጊዜ ወደጊዜ እየሰፋ ከመጣው የኢኮኖሚ ልማት አውታሮች ጋር የተያያዘ ነው፡፡

እንዲያም ሆኖ የአገልግሎቱ ፈላጊ ህዝብ የሚፈልገውን አገልግሎት በተገቢው ጥራትና መጠን ባለማግኘቱ ሮሮ ማሰማቱም አግባብ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ሆኖም ግን የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ችግሩን ለማስወገድ ከሚያደርጉት ጥረት ጎን ለጎን ህዝቡ የችግሩን ምንጭ በተገቢው መንገድ ተገንዝቦ የመንግስት ተባባሪ እንዲሆን የሚኩላቸውን ኃላፊነነት መወጣት አለባቸው፡፡ ከዚሁ ጋርም ሌላው ሊታይ የሚገባው ጉዳይ በአገልግሎት መስጫዎቹ አካባቢ የተሰማሩት ተቀጣሪ ሙያተኞችም ሆኑ የስራ መሪዎች ሆን ብለውም ይሁን በስህተት የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ሳይችሉ ቀርተው ህዝቡ አገልግሎቱን ሳያገኝ ሲቀር ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረጉ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

እነዚህን የመንገስት ሰራተኞች መቅጣት ብቻ ሳይሆን የተወሰደውን የቅጣት እርምጃ በአደባባይ ለህዝቡ ይፋ ማድረግም ይገባል፡፡ የዚህ ዓይነቱ የመንግስትና የህዝብ ግንኙነት ግልጽነትን በማጠናከር፣ የተጠያቂነት አሰራር ስርዓትን በማስፋትና የህዝብን የማወቅ መብት በማረጋገጥ መልካም አስተዳደርን እውን ለማድረግ ብሎም በአገሪቱ የተጀመረውን ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚና ፖለቲካ ግንባታን ዘላቂነት አስተማማኝ መሰረት ላይ ለመጣል ያግዛል፡፡

ይህንን ማድረግ ካልተቻለ ግን ሁኔታው ሆን ተብሎ የተፈጠረና መንግስትም አቅም የሌለው ነው የሚል የሀሳት መልዕክትን በመፍጠር ጉዳዩን የፖለቲካ መጠቀሚያ ማድረግ ለሚሹ አንዳንን የውጭም ሆኑ የውስጥ ኃይላት መሳሪያ እንደመስጠት የሚቆጠር ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ የእንደዚህ ዓይነቶቹ ተግባራት ዓላማ በመንግስትና ህዝብ መካከል ጥርጣሬ እንዲፈጠር ብሎም በመንግስት ላይ አግባብ ያልሆነ ተቃውሞ እንዲያነሳ እንደዚሁም በህዝቡ ውስጥ ተስፋ የመቁረጥ ስሜትን በማነሳሳት ስርዓት አልበኝነት እንዲነግስ ማድረግ ብሎም የሚፈልጉትን ስልጣን መቆናጠጥ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

በአሁኗ ኢትዮጵያ ግን የዚህ ዓይነቱ ህልም እውን ሊሆን የማይችልበት መሰረት ተጥሏል፡፡ አገሪቱን የሚመራው መንግስት ለመልካም አስተዳደር ጥንካሬ መገለጫ የሆኑ አያሌ ተግባራትን በማከናወኑ ኢትዮጵያ ወደአዲስ የእድገትና ለውጥ ምእራፍ መሸጋገር ችላለች፡፡ ባለፉት ሀያ ዓመታት ጊዜ ውስጥ እየተጠናከረ የመጣው ሰላምና እድገት በዜጎች ልብ ውስጥ ከፍተኛ የለውጥ ተስፋ እንዶጎመራ አስችሏል፡፡ ስርዓቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችን ከድህነት ለማውጣት ያስቻለ ከመሆኑም በላይ የአገሪቱ መጠሪያ ሆኖ የኖረውን ድህነት ታሪክ ለማድረግ ከፍተኛ መነቃቃትንና ወኔን ፈጥሯል፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሚታየው የልማት እድገት አመርቂና ተስፋ ሰጪ መሆኑን የዓለምን የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚከታተሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጭምር ምስክርነታቸውን በመስጠት ላይ ናቸው፡፡

የተዘረጋው የፖለቲካ ኢኮኖሚ ስርዓት ድህነትን በመዋጋት ረገድ እያሳየ ያለው ውጤት የሚያበረታታ መሆኑን የአገሪቱ የልማት አጋር የሆኑ የበለፀጉ አገራትና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ሁሉ በመግለፅ ላይ ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ መብቃት የተቻለው መንግስት ግልፅና የላቀ የለውጥ ራዕይ በመቅረፁ፣ ይህንንም ወደተግባር ለመለወጥ ህዝባዊ አመኔታንና ይሁንታን በመቸሩም ጭምር ነው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡

ከዚሁ ጋርም የአገሪቱ መሪዎች አገሪቱ ያላትን እጅግ አነስተኛ ኃብት እንደዚሁም ከተለያዩ አካላት የሚገኘውን የልማት ድጋፍና ብድር ለታለመላቸው ስራዎች በተገቢው መንገድ በማዋላቸው የዜጎች እኩል ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ የሚያደርገው ጥረትም ከዚህ አኳያ ሊነሳ የሚገባው ተግባር ነው የሚል አመለካከት አለኝ፡፡ ይህም የአገሪቱ የልማት አጋሮች የሚሰጡትን ድጋፍ የበለጠ አጠናክረው እንዲቀጥሉበት እያበረታታቸው መሆኑንም በአሁኑ ወቅት እነዚህ አካላት ከአገሪቱ ጋር ያላቸውን ጠንካራ የትብብር ግንኙነት በማየት መግለፅ ይቻላል፡፡

የአገሪቱ የልማት ለውጥና ይህንንም ተከትሎ በዜጎች ላይ በአሁኑ ወቅት እየታየ ያለው ለውጥ መልካም አስተዳደርን ከማረጋገጥ ጋር ተነጥሎ ሊታይ አይችልም፡፡ ምክንያቱም ደካማ መልካም አስተዳደር በተንሰራፋበት አገር ውስጥ የዚህ ዓይነት ለውጥ ማምጣት አይታሰብም፡፡ የመልካም አስተዳደር ጉዳይ ትምህርትን፣ ጤናን፣ የመሰረተ ልማት አውታርን የመሳሰሉ አገልግሎቶችን በፍትሃዊነትና በተገቢው መጠን ለህዝብ ከማቅረብ ጋር በቀጥታ የሚቆራኝ ነው፡፡

የዚህ ዓይነቱ አገልግሎት ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተስፋፋ መሆኑን ዓለም ሁሉ በአደባባይ እየመሰከረ ያለው እውነት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በተጨባጭ የሚቀርበው ማስረጃ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የቀረጸውና በዓለም ውስጥ ያለውን የድህነት መጠን በግማሽ ለመቀነስ ታስቦ እየተተገበረ ያለው የምእተ ዓመቱ የልማት ግብ ነው፡፡ በዚህ አካል ግምገማ መሰረት ኢትዮጵያ በዚህ የልማት ፕሮግራም ውስጥ ከተጠቀሱትና የህዝቦችን እኩል ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ድህነትን ለመቀነስ ያስችላሉ ተብለው ከተቀመጡት ስምንት ግቦች መካከል ትምህርትና ጤናን የተመለከቱትን ማሳካቷን ይፋ አድርጓል፡፡ ሌሎች ግቦችንም ለማሳካት የሚያስችል ጠንካራ መሰረት ላይ መሆኗንም አረጋግጧል፡፡

ዓለም አቀፍ ሪፖርቶች እንደሚገልፁት በኢትዮጵያ ከድህነት ወለል በታች የሚኖረው ህዝብ ቁጥር ከሶስት ዓመት በፊት በነበረ ጥናታዊ አሃዝ መሰረት ብቻ ከአስር በመቶ በላይ በሆነ መጠን ቀንሷል፡፡ የአገሪቱ የግብርና ምርታማነት በእጅጉ በመጨመሩ የተነሳም ዜጎች የምግብ ዋስትና ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ተሻሽሏል፡፡ በዚህም የተነሳ በአሁኑ ወቅት በተፈጥሮ አደጋ በሚከሰት የምግብ እጥረት ሳቢያ ህይወቱ የሚያልፍ ዜጋ የማይከሰትበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

እነዚህ ከፍተኛ እመርታዎች ህዝብ በመንግስት ላይ ያለውን እምነት አጠናክሯል፣ ከፍተኛ የማደግና የመለወጥ መንፈስንም ፈጥሯል፡፡ ያም ሆኖ ግን ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የአገልግሎት አቅርቦት እጥረቶች ጋር በተያያዘ የሚከሰቱትን ክፍተቶች በክፋት መልኩ በመተርጎም ለፖለቲካ ዓላማ ለማዋል ለሚሞክሩት አካላት እድል መስጠት አይገባም፡፡ ይህ ክፍተት ተጨባጭነት ባለውና ከአገሪቱ የለውጥ ሂደት ጋር በተያያዘ የተፈጠረ መሆኑን በግልፅ ለህዝቡ በማስታወቅ የክፋት በሩን በቀላሉ መዝጋት ይቻላል የሚል እምነት አለኝ፡፡ በእኔ ምልከታ የመልካም አስተዳደር ጉዳይ የአገሪቱ ህልውና ጭምር ነው፣ ይህንንም መንግስት ይገነዘባል፡፡ ለዚህም ነው መልካም አስተዳደርን ለማጠናከር በየጊዜው ደፋ ቀና ሲል የሚታየው፡፡